# Center City PCS Extended Day Parent Handbook

Manager of Programs & Partnerships
Allison Jones
202-492-5770
ajones@centercitypcs.org

ሴንተር ሲቲ ፒሲ ኤስ ከትምህርት በፊት እና በኋላ በክፍያ የሚሰጥ የጠዋት የህጻናት እንክብካቤ ፕሮግራም ነው።ፕሮግራሙ ከፕሪኬ ሶስት እስከ 8ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች ክፍት ነው።

ከትምህርት በፊት እንክብካቤ

ከትምህርት በፊት እንክብካቤ ፕሮግራም የሚሰራው ከሰኞ እስከ አርብ የመክፈቻ ሰአት 7:00 am ሲሆን ተማሪዎችን ከ 7:00 - 7:30 am ማድረስ ይቻላል። ተማሪዎችን ከ7:00 am በፊት ማድረስ ወይም ከህንጻው ውጪ ትቶ መሄድአይቻልም። ይህን ማድረግ ለሲኤፍኤስኤ ሪፖርት እንዲደረጉ ወይም ከትምህርት በፊት እንክብካቤ እንዲሰናበቱ ሊያደርግ ይችላል። ከ7:30 am በኋላ የሚመጡ ተማሪዎች እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም። 7:30 am መድረሳቸው

ሁሉም ተሳታፊዎች ቢያንስ ለ 30 ደቂቃ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ማለትም የቤት ስራ ሲሰሩ እገዛን ማግኘት፣ የጠዋትማነቃቂያዎች እና በድህረ ገጽ የሚሰጡ መርጃዎችን ለመጠቀም እንዲችሉ በቂ ጊዜ ይሰጣቸዋል። ወላጆች/አሳዳጊዎችየህንጻው የውስጥ ክፍል ድረስ በመግባት ፈርመው ልጆቻቸውን ለከትምህርት በፊት እንክብካቤ ፕሮግራም ማድረስ
ይጠበቅባቸዋል።

ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ
ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ሃሙስ እና አርብ ከ3:30 pm እስከ 6:00 pm ፤ ዕረቡ ደሞ 1:30 pm -6:00 pm በከፍያ የሚሰጥ ሲሆን፤ ትኩረት የሚያደርገው የቤት ስራን ሰርቶ መጨረስ እና የ ካምፓስ መሪው በሚያወስናቸውማጠናከሪያዎች ላይ ነው። በፕሮግራሙ ወቅት ተማሪዎች የቤት ስራን ለመስራት የተሰጠ በትንሹ 120 ደቂቃ የሚሆንጊዜ በሳምንት ውስጥ ይኖራቸዋል።

ከትምህርት በኋላ የቤት ስራን ማጠናቀቅ
የቤት ስራን ማጠናቀቅ ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ ቡድን እና በቤተሰብ መሃል የሚደረግ የጋራ ጥረት እንደሆነ እናምናለን። ተማሪዎች የቤት ስራቸውን ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ ፕሮግራም ላይ አጠናቀው እንዲመጡ መጠበቅየለበትም። በተለምዶ ፒኬ እስከ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከ 30 እስከ 60 ደቂቃ የሚፈጅ የቤት ስራ እንዲሁም ከሶስተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ደሞ ከ 40 እስከ 75 ደቂቃ የሚፈጅ የቤት ስራ ይመደብላቸዋል።
አብዛኞቹ ተማሪዎች የተሰጣቸውን የቤት ስራ ቢያንስ ግማሹን በከትምህርት በኋላ እንክብካቤ የቤት ስራ መስሪያ ሰአትላይ ከ30 እስከ 45 ደቂቃ በመጠቀም ያገባድዳሉ።

ቤተሰቦች/አሳዳጊዎች ጠዋት ሲያደርሱ እና ማታ ሲወስዱ እንዲፈርሙ ይገደዳሉ።

እንክብካቤ የቤት ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ

የቤት ስራ ማጠናቀቅ በድህረ ኬር ሰራተኞች እና በወላጆች መካከል የጋራ ጥረት መሆን አለበት ብለን እናምናለን። የሚጠበቀው ነገር ተማሪዎች ከእንክብካቤ በኋላ የቤት ስራን እንዲያጠናቅቁ አይደለም። በተለምዶ፣ ከPK-2ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በየቀኑ ከ30 እስከ 60 ደቂቃ የቤት ስራ ይመደባሉ፣ እና ከ3ኛ-6ኛ ክፍል ተማሪዎች ከ40 እስከ 75 ደቂቃ ይመደባሉ። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከ30 እስከ 45 ደቂቃዎች ባለው የቤት ስራ ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ግማሹን የቤት ስራ ማጠናቀቅ ይችላሉ።

አርፍዶ የመውሰድ ፖሊሲ
ልጃቸውን በ6:00 pm መጥተው መውሰድ ያልቻሉ ቤተሰቦች ልጃቸው/ልጆቻቸው ከ 6:00 pm በኋላ ያለዉን የቆዩበትንእያንዳንዱን ደቂቃ ለእያንዳንዱ ልጅ $2 ይከፍላሉ። ይህ ህግ በጽኑነት ይተገበራል።
ይህን ዘግይቶ የመውሰድ ከፍያ ወራዊ ከፍያ በሚደርስበት ወቅት ተጣምሮ ካልተከፈለ ልጆ ከፕሮግራሙ እንዲሰናበት የሚያደርግ ሲሆን። ቆይታውን ለመቀጠል አካውንቱ 0 እስኪሆን ይጠበቃል።ከ6:15 pm በኋላ ልጅን ለመዉሰድመምጣት ለህጻናት እና ቤተሰብ አገልግሎቶች አጀንሲ (ሲኤፍኤስኤ) ሪፖርት እንዲደረግ እና 3 ጊዜ ልጆ እረፍዶከተወሰደ እስከቀጣዩ የትምህርት አመት ከፕሮግራሙ እንዲታገድ ሊያበቃው ይችላል።

ከትምህርት በፊት እና በኋላ እንክብካቤ የአከፋፈል ፖሊሲ
የእያንዳንዱ የተራዘመ ቀን ፕሮግራም ከፍያ ወር በገባ በ15 ነው።ከፍያዉን በተባልው ጊዜ አለማጠናቀቅ የአገልግሎቶችእገዳን ያስከትላል። አካውንቱ 0 እስካልሆነ ድረስ አገልግሎቶቹ
ተመላሽ ያልሆነ የምዝገባ ከፍያ
በተራዘመ ቀን ፕሮግራም ውስጥ ለተመዘገቡ ለእያንዳንዱ ልጅ የማይመለስ $50.00 የምዝገባ ከፍያ ያስፈልጋል። ይህ ከፍያ ልጅዎ በፕሮግራሙ ውስጥ የተመዘገበበት/የተመዘገበችበት የመጀመሪያ የአገልግሎት ጊዜ ወጪ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። የምዝገባ ከፍያው በምዝገባው ወቅት ነው። ቀሪው ሙሉ በሙሉ እስኪከፈል ድረስ በተራዘመ ቀን ፕሮግራም

ውስጥ ምዝገባ ዐልተጠናቀቀም ማለት ነው። እባክዎ የመመዝገቢያ ከፍያ የማይመለስ መሆኑን ያስተውሉ።
በማንኛውም ምክኒያት ልጅዎ ከተመዘገበ/በች በኋላ በተራዘመ ቀን ፕሮግራም ላይ የማይገኝ/የማትገኝ ከሆነ፣
ከፍያው አይመለስም። የምዝገባ ከፍያ በኦንላይን በ EZ ChildTrack በኩል ሊከፈል ይችላል.
እባክዎን ያስተውሉ ፕሮግራሙ ከሞላ እና ልጅዎ በተጠባባቂዎች ዝርዝር ውስጥ ከተቀመጠ/ች የምዝገባ ከፍያ አይከፍሉም። የልጅዎ ስም ከተጠባባቂው ዝርዝር ውስጥ ከወጡ፣ በኢሜል ማሳወቂያ ይደርሰዎታል እና ለኢሜይሉ ምላሽ ለመስጠት እና ሙሉውን ቀሪ ሂሳብ ለማስገባት ሁለት (2) ቀናት ይሰጥዎታል።
ይህንን ፖሊሲ በማክበር ለምታደርጉት ግንዛቤ እና ትብብር እናመሰግናለን። ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካለዎት ወይም

ተጨማሪ እርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎን አሊሰን ጆንስን በ ajones@centercitypcs.org ለማነጋገር አያመንቱ።
ለቀጣይ ድጋፍህ እና የልጆችዎን እንክብካቤ እና ትምህርት አደራ ስለሰጡን እናመሰግናለን።

አይቀጥሉም። ይህም ልጅ ቦታዉን እንዲያጣና ተጠባባቂዝርዝር ላይ ያሉ ቤተሰቦች ቦታውን እንዲያገኙ ሊያደርግ ይችላል።ተማሪው በከፈለበት ወር በመቅረት፣ በቅጣት ወይምበመውጣት፤ እነዚህን እና እነዚህን በመሳሰሉ ምክንያቶች ፕሮግራሙ ላይ መሳተፍ ባይችል የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽአይሆንም ክሬዲትም አይሰጥም። ክፍያ ባለመከፈሉ ምክንያት ከመካፈል የቀረ ልጅ ከትምህርት በፊት እንክብካቤ
ቢመጣ ሲኤፍኤስኤ ሊጠራ ይችላል።ክፍያ ባለመከፈሉ ምክንያት ከመካፈል የቀረ ልጅ ከትምህርት በኋላ እንክብካቤቢመጣ ወደ ትምህርት ቤት ቢሮ የሚላክ ሲሆን ትምህርት በተዘጋ በ 30 ደቂቃ ውስጥ ቤተሰብ ካልወሰደው
ሲኤፍኤስኤ ሊጠራ ይችላል።

<u>ከትምህርት በፊት እና በኋላ እንክብካቤ ክፍያዎች</u>

- ከትምህርት በፊት እንብካቤ ብቻ ከሰኞ እስከ አርብ ፡ በወር ለእያንዳንዱ ልጅ $80
- ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ ረቡዕ ብቻ በወር ለያንዳንዱ ልጅ $65
- ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ ከሰኞ እስከ ሃሙስ ብቻ በወር ለያንዳንዱ ልጅ $175
- ከትምህርት በፊት እና ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ በወር ለእያንዳንዱ ልጅ $190

ክትምህርት በፊት እና በኋላ እክብካቤ  አገልግሎት ለእህት ወይም ለወንድም ቅናሽ አለ?
በተመሳሳይ ፕሮግራም ለሚሳተፉ ተጨማሪ የአንድ ቤት ልጆች የአምስት ፐርሰንት (5%) ቅናሽ አለ።

በ ሴንተር ሲቲ ፒሲ ኤስ የተራዘመ ቀን ፕሮግራም መክፈል የሚቻልባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?
ሴንተር ሲቲ ፒሲ ኤስ ሁሉንም ክሬዲት ካርዶች እና የዴቢት አካውንት ክፍያዎች ይቀበላል። በማንኛዉም ሁኔታ፤ካሽ፣ ቼክ፣ መኒ ኦርደር ወይም ካሸር ቼኮች ተቀባይነት የላቸውም። ሁሉም ክፍያዎች በ EZ Child Track ማስፈንጠሪያ በ https://www.ezchildtrack.com/parent3/ParentLogin.aspx?c=centercitypcs .ሊሆን ይገባል።ሴንተር ሲቲ ፒሲ ኤስ የድጎማ ቫውቸሮችን ለፕሮግራሙ እንደክፍያ አይቀበልም።

ልጄ ለተራዘመ ቀን ፕሮግራም ለተወሰኑ ቀናት ብቻ መመዝገብ ይችላል/ትችላለች?
ልጆ ዕረቡ ዕለት ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ ብቻ በተወሰነ ክፍያ ማእከሉ እንዲመጣ ሊመርጡ ይችልላሉ። ከዛ ወጪ ምዝገባ ለወሩ ባጠቃላይ ነው። ባሰኘ ሰዐት መምጣት እና ክፍያን በማናቸውም ምክንያት ለማመጣጠን መሞከር አይፈቀድም። ወቅታዊ የሆነ የክፍያ መርሃግብሩን ከማእከላዊ ቢሮ ይጠይቁ።

ልጄን እንዴት ወደተራዘመ ቀን ፕሮግራም ማስገባት እችላለሁ?
የተራዘመ ቀን ፕሮግራም ውስጥ ልጃቸውን ማስገባት የሚፈልጉ ቤተሰቦች EZ Child Track ( https://www.ezchildtrack.com/parent3/ParentLogin.aspx?c=centercitypcs ).ላይ በመግባት መመዝገብ ይኖርባቸዋል። ለመመዝገብ እገዛ የሚያስፈልጎት ከሆነ የ ካምፓስ ኦፐሬሽን ስራ አስኪያጅን ያናግሩእንደ አስፈላጊነቱ ጠሪዎን ያስተናግዳሉ። የድህረ ገጽ ምዝገባዉን ማከናወን እና ወርሃዊ ክፍያዉን በተገቢው ጊዜ በየአንዳንዱ ወር መክፈል ልጆ ቦታውን ጠብቆ እንዲዝልቅ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል።
ልጄን ከተራዘመ ቀን ፕሮግራም ማስወጣት እችላለሁ?
ልጃቸውን ከየትኛዉም የተራዘመ ቀን ፕሮግራም ለማውጣት የሚፈልጉ ቤተሰቦች የውል ማፍረሻ ፎርሙን መሙላት ይጠበቅባቸዋል። ፎርሙ በድህረ ገጻችን https://x6kc0b.p3cdn1.secureserver.net/wp-content/uploads/2019/07/19-20Before-Care-After-Care-Cancellation-Form-1-1.pdf. ላይ ይገኛል። ሁሉም ያገልግሎት ለውጦች በቀጣዩ ወር ክፍያ ውስጥ እንዳይገቡ አገልግሎቱን ማቆም ከተፈለገበት ወር በፊት ባለው ወር 16ኛ ቀን መፈጸም ይኖርባቸዋል።(ለምሳሌ:- የጥቅምትን አገልግሎት ለመሰረዝ የውል ማፍረሻ ፎርሙ ተሞልቶ በመስከረም 16 ሊቀርብ ይገባል) ይህን የማያደርጉ ቤተሰቦች ልጃቸው ፕሮግራሙን ተከታተለም አልተከታተለም የቀጣዩን ወር ክፍያ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። ፎርሙ ተሞልቶ እንዳለቀ ለካምፓስ ኦፐሬሽን ስራአስኪያጅ ኮፒ መስጠት ወይም ለወ/ሮ አሊሶን ጆንስ በ ajones@centercitypcs.org ኢሜል ማድረግ ይቻላል።

ልጄ የገባበትን የተራዘመ ቀን ፕሮግራም እንዴት መቀየር እችላለሁ?

አካውንታቸው ላይ አገልግሎቶችን መጨመር ወይም መቀነስ የሚፈልጉ ቤተሰቦች የአገልግሎት መለወጫ ፎርም መሙላት አለባቸው። ፎርሞቹ በድህረ ገጻችን https://x6kc0b.p3cdn1.secureserver.net/wp-content/uploads/2019/07/19-20After-Care-Change-of-Services-form-1.pdf. ይገኛሉ። ፎርሙ ተሞልቶ እንዳለቀ ለካምፓስ ኦፕሬሽን ስራ አስኪያጅ ኮፒ መስጠት ወይም ለወ/ሮ አሊሶን ጆንስ በ ajones@centercitypcs.org ኢሜል ማድረግ ይቻላል።

ትምህርት ቤት ከተዘጋ ፣ አርፍዶ ከተከፈተ ወይም በጊዜ ካለቀ ከትምህርት በፊት እና በኋላ እንክብካቤ አገልግሎት ክፍት ይሆናል?
ትምህርት ሲዘጋ ወይም በአል ሲኖር ይህ አገልግሎት አይሰጥም። ረፍዶ ትምህርት በሚጀመርባቸው ጊዜያት ከትምህርት በፊት እንክብካቤ አገልግሎት ባይኖርም ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ አገልግሎት ግን ይሰጣል። ከትምህርት በኋላ የሚሰጥ እንክብካቤ በአደጋ ወይም በአየር ሁኔታ ምክንያት ትምህርት ቤት በጊዜ ከተዘጋ አገልግሎት አይሰጥም።

ቁርስ ወይም መክሰስ ታቀርባላቹ?
ከትምህርት በፊት እንክብካቤ ቁርስ አያቀርብም። ቁርስ የሚቀርበው መደበኛው የትምህርት ቀን ሲጀምር ነው። ከትምህርት በኋላ እንክብካቤ ደግሞ በ ፕሮግራሙ ሰአት መክሰስ ያቀርባል።